# “ዲሞክራሲ በትግላችን…” አምባገነናዊ ዜማ

ታሪኩ አባዳማ ህዳር 2004

*እንደ መለስ የቅርብ ግዜ አነጋገር ከሆነ ‘አሁን የጨበጥኩትን መብት የተጎናፀፍኩት ታግዬ ነው’ - ማንም (ጠ/ሚኒስትርነቱን) ስላልመፀወተኝ ማንም ሊቀማኝ አይችልም - ስለዚህ ‘መብቴ ተደፈረ  የምትል ታግለህ ተቀዳጅ’ ሲል - ‘ዲሞክረሲ’ በትግል ብቻ እንደሚረጋገጥ እቅጩን ነግሮናል።*

*‘የዲሞክረሲ’ መብት በትግል እንጂ ከመንግሰት በሚታወጅ ደንብ ወይንም በመለስ አባባል ‘በልመና አይገኝም’ ተብሏል። ለመለስ የዲሞክረሲ መብት ማለት በህግ በላይነት ላይ የተመረኮዘ ማህበራዊ እና አገራዊ ልዕልና ሳይሆን ጠመንጃ አንግቦ ከመንግስት ጋር የተፋለመ እና ያሸነፈ ሁሉ ይገባኛል በሚለው ልክ የሚቀዳጀው የደም ዋጋ ነው - ጉማ ነው።*

*በህወሀት ውስጥ ተደራጅቶ መራራውን ትግል ያራመደው የትግራይ ወጣት አዛውንቱ ፣ ሴት እና ወንዱ ሆ ብሎ ዘገር የነቀነቀው አንድ ግለሰብ በጠ/ሚኒስትርነት ማዕረግ መላ አገሪቱን አፍኖ እንዲገዛ ነበር ማለት ነው? ወይስ መለስ በግሉ ባደረገው የትግል አስተዋፅዖ ድርሻው የጠ/ሚኒስትርነት ወንበር ለዘላለሙ የሚያሸልም ነበር?*

*ግራም አሉት ቀኝ እነ መለስ የተቀዳጁት ዲሞክራሲያዊ መብት ወደ ተግባር ሲመነዘር ጠ/ሚኒስትር… ሆኖ ያሻውን በማድረግ አለመጠየቅ እና አለመከሰስ መብት ነው። ያገር ሀብት የመዝረፍ መብት ፣ ህዝብን በጎጥ ከፋፍሎ የመግዛት መብት ፣ ዜጎችን በዘፈቀደ ወህኒ የማጎር መብት ፣ ብሔራዊ ውርደትን የማረጋገጥ መብት… ሲሻው ፕሬዜደንት ሲሻው ጠ/ሚኒስትር የመሆን መብት።*

*የመለስ ዜናዊን አባባል ከልብ ሳጤነው አቋሙ በ*1969 *አጋማሽ ግድም በደርግ ዘመን በዲሞክረሲ መብቶች መረጋገጥ ዙርያ ተነስቶ የነበረውን ውዝግብ መንግስቱ በምን መልኩ አስተናግዶት እንደነበር ያስታውሰኛል። መኢሶን እና ኢጭአት የተባሉ ድርጅቶች ‘ዲሞክረሲ መብት ለጭቁኖች ያለገደብ አሁኑኑ*!!’ *ሲሉ የደርግ ፓርቲ ሰደድ እና አንድ ሰሞን ወዳጅ አድርጎ ያቀረባቸው እነ ወዝሊግ የለም ‘ዲሞክረሲ ለጭቁኖች በትግላችን*!!’ *የሚል መፈክር ይዘው በተፃራሪ ቆሙ።*

1969 *ዲሞክረሲ በትግላችን*!! *መንግስቱ ሃ/ማርያም* — 2004 *ዲሞክረሲ በትግላችን*!! *መለስ ዜናዊ።*

*መንግስቱ ሃ/ማርያም ያን ግዜ ግራ እጁን አያወናጨፈ ‘ዲሞክረሲ መብት በትግላችን’ ብሎ ሲደነፋ እንደኔ ያለው ዜጋ ግራ ተጋባ። ዲሞክራሲያዊ መብታችንን አፍኖ የያዘው በመንግስት ስልጣን ላይ ያለው ገዢ አካል ደርግ መሆኑ ግልፅ ሆኖ ሳለ መፈክሩን ‘በትግላችን’ እያለ ማስተጋባቱ ማን ከማን ጋር ታግሎ ነው ይህ መብት የሚረጋገጠው የሚል ውዥንብር ውስጥ ከተተን።*

*የዜጎች መብት በህግ በድንጋጌ - በጋራ ውይይት እና መግባባት የሚፀድቅ እንደመሆኑ ይህን ለማስፈፀም የሚያስችለውን የመንግስት ስልጣን ይዞ ያለው ሀይል እራሱ ‘በትግላችን’ ማለቱ ምን የሚባል ፈሊጥ ነው ብለን ተደናገርን። ያንን የደርግ አስከፊ ስርዓት ገረሰስኩ የሚለው ወያኔ እነሆ ከአርባ ዓመታት በሁዋላ ‘ዲሞክረሲ በትግላችን’ ብላችሁ ፈክሩ ብሎ እያላገጠብን ነው።*

*በዚያ ሰሞን ደግሞ ጠ/ሚኒስትሩ ኖርዌይ ላይ ላንድ ጋዜጠኛ ሲናገር ‘በአሁኑ ወቅት ኢትዮጵያ ዲሞክራሲ የሰነፈነባት አገር ናት’ አለ። ለፈረንጆቹ የሚነግረው እና ለኛ የሚያስታቅፈን መፈክር እጅጉን ተፃራሪ መሆኑን ልብ በሉ - ለነሱ ዲሞክረሲ የሰፈነባት አገር መስርቻለሁ ይላቸዋል - ለኛ ደግሞ ግፋ! ታገሉ እያለን ነው።*

*‘አሁንስ መንግስቱን መሰልከኝ’ ነው ያሉት ነጋሶ ጊዳዳ (ነጋሲ ግደይ ይባሉ በነበረ ዘመን)።*

*የኖርዌይ ጋዜጠኛ አገዛዝህ በሰብአዊ መብት ጥሰት ይወገዛል ቢለው “በቀድሞው ሥርዓት ዜጎች ተገድለው ቤተሰቦቻቸው ለተገደሉበት የጥይት ሒሳብ እንዲከፍሉ ይገደዱ ነበር” የሚል መልስ ነበር የሰጠው። በደርግ ዘመን ዜጎች ተገድለው ቤተሰቦች የጥይት ዋጋ ይጠየቃሉ - በወያኔ ዘመን ግድያ በነፃ ነው ፣ ወያኔ የጥይት ዋጋ አያስከፍልም*!! *ይገድላል እሬሳ በነፃ ለቤተሰብ ያስረክባል። እንዲህ አይነት ዲሞክረሲ ፣ እንዲህ አይነት አሟሟት  - እንዲህ ያለ ስር ነቀል ለውጥ ያጎናፀፈን አስተዋይ ጠ/ሚኒስትር ‘ቅንድብህ ያምራል’ ተብሎ ቢዘፈንለት ምን ይቆጫል። … ሌላ ምን ይባላል?*